- 33 -

የሰው ልጅ እና የጭካኔው ገፅታ

ባለፈው ሳምንት ውጭ የምትማረው እህቴ ደውላ ነበር። የምትማረው በሙስሊም አገር ነው። ከሷ ስለ ትምህርቷና ስለ ማኅበረሰቡ አጠቃላይ ሁኔታ ለመስማት ጓጉቼ ነበር። ስለ ሁኔታዋ ከተጠያየቅን በኋላ ስለ አዲሱ አገሯ ጠየቅኳት። በሙስሊም አገር መኖር ሁሉ ነገሩ አስደሣች ሊሆን እንደሚችል አሰብኩ። ግና እሷ የገለፀችልኝ ነገር አስደነገጠኝ። ሴት ልጅ ከቤቷ ወጥታ በወንዶች የማትለከፍበት አንድም ቦታ የለም ለማለት እንደሚያስደፍር ነገረችኝ። ይህ ሁኔታ ለአንድ የተወሰነ አካባቢ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ቦታ ሊባል በሚያስችል መልኩ የተስፋፋ መሆኑን ገለፀችልኝ። ስለ አንዲት ስለምታውቀው ሙስሊም ሴትም ነገረችኝ። እሷን ባየችበት አጋጣሚ ልጅቷ ታከሲ እየተሳፈረች ነበር። ለሾፌሩም የታከሲ ሂሳቡን ሠጠችው። በነኚህ አገራት የተጓዙበትን ርቀት የሚገልፅ ጥብቅ የሆነ መለኪያ የለም። ስለሆነም ከፍያው በስምምነት የሚፈፀም ስለሚሆን አለመግባባት ተፈጥሮ ሾፌሮች የሚናደዱበት ሁኔታ ይኖራል። በከፍያው የማይስማሙ ከሆነ ንትርኩ ተባብሶ ሾፌሮች ከሴቷ ጭምር ጋር የሚያያዙበት ሁኔታ ይፈጠራል። በርግጥም ከልጅቷ ጋርም የሆነው ያ ነው። ሾፌሩ ሲይዛት ልጅቷ ተናዳ ከሾፌሩ ጋር ግጭት ውስጥ ገባች። ሾፌሩም ወጣቷን ልጅ በጥፊ መታት።

ታሪኩን ስትነግረኝ በጣም ተረበሽኩ፣ ተናደድኩም። እህቴ እንደነገረችኝ ቀጥሎ የመጣው ነገር የከፋ ነበር። በቅርበት ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩ ወንዶች ነበሩ። ወደ ቦታው በመሮጥ በተፈጥሮም እንደሚደረገው ልጅቷን አገዟት ልላችሁ አይደለም።

ግና እዚያ ደርሰው ግብግቡን ቆመው መመልከት ጀመሩ።

ይህ ታሪክ ነው እንግዲህ ትልቅ ግርምት ያጫረብኝ። ወዲያውኑ "ወንድነት" ማለት ምን ማለት ነው የሚለውንና የማላምንበትን እያንዳንዱን ትርጉሞች ማጤን ጀመርኩኝ። አንድ ወንድ ያውም ሁለትና ሦስት ሆነው ከዚያም በዛም ብለው ሴት ልጅ ስትጠቃ ቆመው ያያሉ። በዛሬው ማኅበረሰብ ውስጥ ወንድነት ማለት እንዴት ነው የሚገለፀው በማለት ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ። ምን ማለት ነው? ወንድነት ሙሉ ትርጉሙ ጠፍቶ አሊያም ተሸራርፎና ተቀናንሶ ለዶታ መገለጫ ብቻ የሚውል ሆነ እንዴ?

እኛ እንደ ሙስሊም ለ"ወንድነት" የምንሠጠው ትርጉም ምንድነው? የኛም ትርጓሜ ከነርሱ ጋር ተመሳስሎብን ከሆነ ይገርመኛል። ዛሬ ላይ ወንድ ሲባል ትዕግስት የሌለው፣ ስሜቱን የማይገልጽ፣ የማያዝን፣ ኃይለኛ እና ወደኋላ የማይል ሆኗል ትርጉሙ። አካላዊ

CamScanner

CamScanner

ጥቃት ማድረጉ ይበረታታል። ወንድ ሆኖ የውስጥ ስሜትን (እንባን፣ እዝነትን፣ ልስላሴን) ማሳየት ይጠላል። ግና ወንድነት ምን እንደሆነ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አስተምህሮ መረዳት ይኖርብናል። መመልከት ያለብን እርሣቸውን ነው።

ዛሬ ላይ ለሰውነት አሊያም ወንድነት ከሚሠጡ የተለመዱ ትርጉሞች መካከል አንዱ የውስጥ ስሜትን ያለመግለጽ ሁኔታ ነው። ማልቀስ ወንድነት እንዳልሆነ እና የደካሞች ባህሪ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አመለካከት ግን ከዚህ የተለየ ነው። በሞት አፋፍ ላይ የነበር የአንድ ሴት ልጃቸው ልጅ በተሠጣቸው ጊዜ ዐይኖቻቸው በእንባ ራሱ። ባልደረባቸው ሰዕድም "ይህ ምንድነው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሆይ!" አላቸው። እርሣቸውም "ይህ አላህ (ሱ.ወ.) በባሮቹ ልቦና ውስጥ ያስቀመጠው እዝነት ነው። አላህም ከባሮቹ መካከል የሚያዝንላቸው አዛኝ ለሆኑት ነው።" አሉት (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

ዛሬ ግን ወንድ ልጅ የሐዘን ስሜቱን መደበቅ ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም ስሜቶቹን እንዳይገልጽ ዘንድ ገና ከልጅነቱ ተምሮ ያድጋል። በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘመን የዚሁ ዓይነት አመለካከት የነበራቸው ሰዎች ነበሩ። የሆነ ጊዜ አንድ የገጠር ሰው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ወዳሉበት መጣ። እርሣቸውም የልጅ ልጃቸውን (የፋጢማን ልጅ) ግንባሩን ሲስሙት አየ። ገጠሬውም ሰውዬ በሁኔታውና ባየው ነገር በመገረም "እኔ አሥር ልጆች አሉኝ። ግና አንዳቸውንም ስሜ አላውቅም።" አለ። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ሰውዬው በመመልከት "(ለሌሎች) እዝነት የሌለው ሰው (በአላህ) አይታዘንለትም።" አሉ። (ቡኻሪ ዘግበውታል።)

እዝነትንና ከማሳየት አንፃር የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በጣም ግልፅ ናቸው። አቡ ዳውድ እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)፦ "አንድ ሰው የእምነት ወንድሙን የወደደው እንደሆነ እንደወደደው ይንገረው።" ብለዋል።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለሚስቶቻቸው ትልቅ ፍቅር እና እዝነት ነበራቸው። ኢማም ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ እናታችን ዓኢሻ (ረ.ዐ.) እንደምትለው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ምግብ መመገብ ደስ የሚላቸው እርሷ ከርሣቸው አጠገብ የተቀመጠች እንደሆነ ነው። የሚጠጡትም ከአንድ ኩባያ ነው። ኩባያውንም ከንፈሯ ኩባያው ላይ በረፈበት በኩል ነው አዙረው የሚጠጡት። ተመሳሳይ አጥንትም ነው የሚግጡት። እርሷ ከጋጠች በኋላ ይግጣሉ። አሁንም ከንፈራቸውንና ጥርሣቸውን የሷ ከንፈርና ጥርስ ባረፈበት በኩል ያሳርፋሉ። በዚህ መልኩ አንድ አጥንት ይቀባበላሉ።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ቤት ውስጥ ሚስቶቻቸውን ያግዛሉ። ዛሬ ግን ወንድነት ነው ተብሎ የምናየው ነገር የቤት ውስጥ ሥራ ሴቶችን ብቻ እንደሚመለከት ተደርጎ

CamScanner

CamScanner

ነው። ዓኢሻ (ረ.ዐ.) እንዳወሩልን "የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ጫማቸውን ይጠግኑ፣ ልብሳቸውን ይሰፉ፣ ፍየሎቻቸውን ያልቡ፣ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ሚስቶቻቸውን ያግዙ ነበር።" (ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት)

ዛሬም ድረስ በስፋት ያለው አስተሳሰብ ወንድ ልጅ እንደ ወንድነቱ ኃይለኛ መሆን እንዳለበት ነው። ልስላሴና እዝነት ማለት በብዙዎች ዘንድ ከሴትነት ባህሪ የሚመደብ ነው። ግና የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል "አላህ አዛኝ ነው፤ እዝነትን ይወዳል። በሻካራነትም ሆነ በሌላ ነገር ውስጥ ያላደረገውን ጥቅምም በእዝነትና ልስላሴ ውስጥ አድርጓል።" ብለዋል። (ኢማም ሙስሊም እንደዘገቡት)

በሌላም ሐዲሣቸው "እዝነትና ልስላሴን የተነፈገ መልካም ነገርን ተነፈገ።" ብለዋል። (ኢማም ሙስሊም እንደዘገቡት)

የዚህ ዓይነቱ ሞገስ ከኛዎቹ የዘመናችን የወንዶች ወንዳ ወንድነት ባህሪ ጠፍቷል። አንድ ወጣት በመንገድ ላይ ሴት ልጅን መጎንተልን እንደ ወንድነት ሲቆጥረው ማየት ያበሳጫል። ሴት ልጅ ስትጠቃ ቆሞ የሚያይ ወንድ እንዴት ራሱን ሰው አድርጎ ሊቆጥር ይችላል? ከነቢያዊ ተምሳሌትነት በላይ የሆሊውድን ጋንግስተሮች እንደ "ወንድ" መለኪያነት የምንጠቀም ከሆነ በርግጥም የኛ የሙስሊሞች ሁኔታ ያሳዝናል፤ ይገርማልም።

CamScanner

CamScanner

ምዕራፍ አራት - ሕዝበ ሙስሊም

- 34 -

ቅጥያውን አስወግዱ

አንተ ምን ዓይነት ሙስሊም ነህ/ሽ? ጥያቄው ትንሽ ለየት ይላል አይደል? ...ግና እስልምናን ለመከፋፈልና ለመውረር ለሚፈልጉቱ የዚህ ጥያቄ መልስ እጅጉን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ከነርሱ ይልቅ በጣም የሚረብሸው ደግሞ እኛ ለርስ በራሣችን የሠጠናቸው ስያሜዎች ናቸው።

ሌላው ቀርቶ በቤተሰባችን ውስጥ እንኳ የምንስማማ ጥቂቶች ነን። የተለያየ ሥም ተሠጣጥተናል። አንድ የቤተሰብ አባል ትልቅ ስህተት የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ ከኛ የተለየ አመለካከት ካራመደ፤ ከዚያ ቤተሰብ መለየት የምንፈልግና ሥማችንን መቀየር የምንፈልግ በርካቶች ነን። ዛሬ በኛ ሙስሊም ቤተሰቦች መካከል ይኸው ነገር ትከከል ሆኖ የታየኛል።

ዛሬ እኛ ሙስሊሞች እንጂ ሌላ አይደለንም። በኛ ውስጥ ሌሎች አካላት የሠጡን የተለያዩ ሥሞች አሉ። አንዳንዶቻችን ሥሙን ስለተቀበልን፤ ብንጠየቅ ከኢስላም ሥም ውጭ እንዲህ ነን ብለን በዚያ ሥም ለመመለስ እንኳን አናመነታም።

በርግጥ በሙስሊሞች መካከል የሚታዩ ክፍፍሎች ይኖራሉ። ግና በጣም ትክክል ያልሆነ ነገር በማኅበረሰባችን ውስጥ ተከስቷል። በኢስላም ማዕቀፍ ውስጥ ልዩነቶችን መቀበልና መቻል ብቻ ሳይሆን እንደ አላህ እዝነት ማየትና ማበረታታት ነው የሚያስፈልገው። ግና ከኛ ጋር የማይግባቡትን ወዲያ ወደ ጠርዝ በገፉን ቁጥር ውድቀታችን ከዚያ ይጀምራል። ይህንን ክፍፍል እንደ ሀብታችን እና ማንነታችን እስካልተቀበልን ድረስ ውጤቱ ውድቀት ብቻ ነው የሚሆነው።

በከፍፍል የተነሳ እያንዳንዳችን የየራሣችን የሆነ ቡድን ፈጥረናል፤ የራሣችን ስብሰባና ኮንፈረንስ ብቻ የምናካሂድበት ቦታ አለን። ከዚያ በኋላ ከኛ ጋር ከሚግባቡትና ከሚስማሙት ጋር ብቻ ማውራት እንጀምራለን። ይህ ሲሆን በሙስሊሙ መካከል መነጋገር የሚባለው ነገር ይጠፋል። ልዩነቶቻንን ጫፍና ጫፍ ይሄዳል፤ ጠርዝ እና ጠርዝ ይሆናሉ፤ አመለካከታችንም ጽንፍ ይረግጣል። ከዚያ በፊት በሂደትም ግን ከኛ ቡድን ውጭ ናቸው ባልናቸው በሌሎች ዓለም በሚገኙ ሙስሊሞች ላይ ስለሚደርሰው ነገር መጨነቅ እናቆማለን። የዚህ ዓይነቱ አካሄድ እግርና እጅን ከዋናው ሰውነት ከፍል

CamScanner

CamScanner

ከመቆራረጥ ተለይቶ የሚታይ መሆን የለበትም። የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) ይህንኑ ነው ያስተማሩን። ሌሎች (አሁንም ወንድሞቻችን ለመሆን የሚፈልጉትን) እኛ ከነርሱ ጋር መጠራት ስለማንፈልግ የውጭ ሰው አድርገናቸዋል። በአንድ የቤተሰብ ሥም መጠራት እንፈልግም:: እነሱን ንቀን ገፍተናቸዋል። ሌላው ቀርቶ ጠላት ሁሉ ከነርሱ አንባር ልንደግፍ እንችላለን።

በከፍፍልና ሥም በመሠጣጠት ምክንያት የሆነ ጊዜ እንተዛዘን የነበርን ሰዎች ድንገት ጠላት እንሆናለን። እርስ በርሣችን ተደካከመን ጠላት እስልምናን የሚያሸንፍበት መሣርያ እንሆናለን። ጠላቶቻችን በነቢዩ ሐዲሥ እንደተጠቀሰው ግዳይ እንዳገኘ አውሬ ሊበሉን ይጠራሩብናል። በብዛት እንበልጣቸዋለን ግና ደካሞች እና የተበታተን በመሆናችን ነው።

በማርች 18/2018 የአሜሪካው ተጽእኖ አሳዳሪ የአሰላሳይ ቡድን (RAND) ባወጣው ሪፖርት እስልምናን በምዕራቡ ዓለም ኢ-አማኒነት ውስጥ እንዲጠፋ በማድረግ እና እንደገና በመልሶ በመሠራት ወደ ሥልጣኔ ማሳደግ ይቻላል ብሏል። በሪፖርቱ እንደተጠቀሰው የሰለጠነውን ዲሞክራሲያዊ ኢስላም ለመመሥረት፣ ባለድርሻ አካላት፣ የተለያዩ የሀብት ዓይነቶች፣ የሰው ኃይል፣ የመረጃ ምንጮች፣ እና ስትራቴጂ ይፈልጋል። ቼሪል ብራንድ እንዲህ በማለት ጽፏል:- ዘመናዊነት ወግ ልማድን ማራመድ አይደለም። ለምዕራቡ የሚሠራ ስትራቴጂ መሆን አለበት። ይህም ሲባል ከባህል መነጠልን፣ ማሻሻልን፣ እንዲሁም የሃይማኖቱን ትክክለኛና እውነተኛ የአስተምህሮ ክፍሎችን መርጦና ሆነብሎ መተውን ያጠቃልላል።" ብሏል።

ሰዎችን ከኢስላም ለመነጠል፣ እምነቱን ለማሻሻል፣ ለመቀየር እና ሆነ ብሎ የተመረጡ አስተምህሮዎችን መዝለልን በተመለከተ በርናንድ ቀላል ነው ያለውን ስልት እንዲህ በማለት ትጠቁማለች - ሥም መስጠት፣ መከፋፈል እና መቆጣጠር። ለያንዳንዱ የሙስሊም ቡድን ሥም ከሠጡ በኋላ አንዱን በሌላኛው ላይ ማነሳሳት ይቻላል።" ብላለች።

በርናንድ ሌሎች መንገዶችን ስትጠቁም "በወግ አጥባቂዎችና በሃይማኖት አክራሪዎች መካከል ልዩነት መፍጠር በሁለቱ መካከል አንድነት እንዳይፈጠር ማድረግ ነው።" ትላለች።

ይህንን ከፍፍል በማሳካት ዘመናዊ/ ተራማጅ የሆነ ሙስሊም መፍጠር ይቻላል። በዚህ መልኩ ከኋላቀርነት የተላቀቀ፣ ችግር ፈጣሪ ያልሆነ የሠለጠነ ዲሞክራሲያዊ ኢስላምን መፍጠር ይቻላል ትላለች። በተለይ ደግሞ በዚህ መልኩ አዲስ ወግ አጥባቂ ለሆነ ቡድን ራሱን የሚያስገዛ ኢስላም መፍጠር ይቻላል የሚል ተስፋ አላት።

CamScanner

CamScanner

ስለሆነም አስልምናን የማበላሸት የመጀመርያው እርምጃ የሚጀምረው በሥም መሠጣጠት መሆኑን ልናውቅ ይገባል። ለዚህም ይሆነን ዘንድ የአላህን ትዕዛዝ አጥብቀን መያዙ ግድ ይሆንብናል።

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَٱعْتَصِمُوا۟ بِحَبْلِ ٱللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا۟ ۚ وَٱذْكُرُوا۟ نِعْمَتَ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنتُمْ أَعْدَآءً فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُم بِنِعْمَتِهِۦٓ إِخْوَٰنًا وَكُنتُمْ عَلَىٰ شَفَا حُفْرَةٍ مِّنَ ٱلنَّارِ فَأَنقَذَكُم مِّنْهَا ۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمْ ءَايَٰتِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ ﴾

‹‹የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁሳችሁም ያዙ። አትለያዩም። ጠበኛችም በነበራችሁ ግዜ በእናንተ ሳይ (የዋለውን) የአላህን ፀጋ አስታውሱ። በልቦቻችሁም መካከል አስማማ። በጸጋውም ወንድማማቾች ሆናችሁ። ከእርስዋም አዳናችሁ። እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አላህ ለናንተ አንቀፃቹን ያብራራል›› (አሊ ዒምራን : 103)

በዚህ መልኩ ብቻ ነው ምዕራባውያን ካዘጋጁልን የከፍፍልና የማዳከም ወጥመድ ልናመልጥ የምንችለው። ሀሳባቸው ጊዜ ያለፈበት መሆኑን ለማሳየት በያለንበት ሁሉ የተሰበረ ግንኙነቶቻችንን ልንጠግን ይገባል።

ሌላው ደግሞ "ዘመናዊ" ወይም "ሚዛናዊ" መባል ምናልባት ቃሉ ሊማርከን ይችላል። ይህንን ሰዎች በተደጋጋሚ እንዲህ ሁኑ በማለት እየነገሩን ሊያታልሉን ቢሞክሩ እንኳን ጆሮ ልንሠጣቸው አይገባም። ኢስላም ትርጉሙ በመሠረቱ ሚዛናዊነት ነው። ስለሆነም መሠረታዊ የሆኑ አስተምህሮዎቹን አጥብቀን በያዝን ቁጥር የበለጠ ሚዛናዊ እንሆናለን ማለት ነው። ኢስላም ጊዜና ቦታ የሚገድበው ሃይማኖት አይደለም። ዓለማቀፋዊ ነው። ስለሆነም እኛ ትክክለኛ ሙስሊሞች ከሆንን ዘመናዊዎቹ ነን ማለት ነው።

እኛ ተራማጆችም፣ ወግ አጥባቂዎችም፣ አዲሶቹ ሰለፊዎችም፣ ፅንፈኛ ሙስሊሞችም፣ ነባሮችም፣ ወሃቢዮችም፣ ስደተኞችም፣ ቀደምቶችም አይደለንም። እናመሰግናለን። እናንተ የሠጣችሁን ቅጥያ አያስፈልገንም። እኛ ሙስሊሞች ነን።

ሙስሊሞች።

CamScanner

CamScanner